02

5ኛ ዓመት ቁጥር 43
5st Year N° 43

ባሕር ዳር የካቲት 30/1992 ዓ.ም.
Bahir Dar 9th March 2000

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL EMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 4.95	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባቂነት የወጣ	የፖ.ሣ.ቁ. 312 P.O.BOX

አዋጅ ቁጥር 43/1992 በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ማዘጋጃ ቤቶችን ለማቋቋም እንደገና ለማደራጀት፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ገፅ 23	Proclamation No 43/ 2000 A Proclamation to Provide for the Establishment, Reorganization and Definition of Powers and Duties of the Municipalities of the Amhara National Regional State Page 23

አዋጅ ቁጥር 43/1992
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ማዘጋጃ ቤቶችን ለማቋቋም እንደገና ለማደራጀት፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

ከተሞቹ ምቹ ሁኔታ ከተፈጠረላቸው የክልሉን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት በማፋጠን ረገድ ጉልሕ ሚና ሊጫወቱ፣ በጋራ የመሥራት ባህልን ሊያዳብሩ፣ ለዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ተግባራዊነት የላቀ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱና በመንግሥትና በህዝብ መካከል ውጤታማ ግንኙነት ለመፍጠር እንደመሣሳል ሆነው ሊያገለግሉ እንደሚችሉ የታመነበት በመሆኑ፣

ይሁን እንጅ በየነኝነት በቀደምት አገዛዞች የተማከለ ሥርዓት ሳቢያ የአማራ ክልል ከተሞች እንደ ሌሎች የሀገሪቱ ከተሞች ሁሉ ከፍ ብሉ የተጠቀሱትን እሴቶች እውን ለማድረግ የሚያስችላቸው የተመቻቸ ህጋዊ ሁኔታና አቅም ለማግኘት ሳይታደሉ መቆየታቸው በመታወቁ፣

በተቃራኒው ባልተማከለ የመንግሥታዊ ስልጣን ድልድል ፖሊሲ ላይ የተመሠረቱት ህገር አቀፍ የኢፌዴሪ እና የአማራ ብሔራዊ ክልል ህገጋት መንግሥታት ለከተሞች ሁለንተናዊ እድገት የተመቻቸ ህጋዊ ሁኔታ መፍጠራቸው በመረጋገጡ፣

የዚሁ ምቹ ህገ መንግሥታዊ መሠረት

PROCLAMATION NO 43/ 2000
A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT, REORGANIZATION AND DEFINITION OF POWERS AND DUTIES OF THE MUNICIPALITIES OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE

WHERE AS, it is believed that urban centres could under favourable conditions play a significant role in the acceleration of social and economic development of the region; enhance Co-operation, promote the exercise of democratic governance and serve as an effective medium in the establishment of a fruitful relationship between the Government and the people;

WHERE AS, however, due mainly to the policy of centralization of the previous regimes, urban centres in the Amhara National Regional State like the rest of the urban centres in the country, did not enjoy the legal environment and capacity to realize the aforementioned values;

WHERE AS, the constitutions of the FDRE and the Amhara National Regional State that rest on the policy of decentralization have now created an enabling environment for an all-rounded municipal development.

WHERE AS, it is necessary to enact and

321

~~78~~ 321 ~~321~~ ~~345~~

በሚገባ ተጠቅሞ በክልሉ አንደ አጠቃላይ የማዘጋጃ ቤቶች ህግ አውጥቶ በሥራ ላይ ማዋል በማስፈለጉ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ም/ቤት በብሔራዊ ክልሉ ህገ መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3.1 ላይ በተሰጠው ህግ የማውጣት ስልጣን መሠረት ከዚህ በታች የተመለከተውን አዋጅ አውጥቷል።

ምዕራፍ አንድ
ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

«ይህ አዋጅ የማዘጋጃ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 43/1992 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ

1. «ቢሮ» ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ነው።
2. «የከተማ ሥራ አስኪያጅ» ማለት የዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 በሚደነግገው መሠረት የሚሾም /የምትሾም/ የማዘጋጃ ቤት ዋና አስፈጻሚ ሹም ነው /ናት/
3. «ሚኒስቴር» ማለት የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ነው።
4. «ከተማ ነክ ጉዳዮች» ማለት የዚህ አዋጅ አንቀጽ 26 በሚደነግገው መሠረት ከተማ ነክ ፍ/ቤቶች የሚዳኟቸውና ሙሉ በሙሉ በነርሱ ስልጣን ስር የሚወደቁ ጉዳዮች ናቸው።
5. «የከተማ ም/ቤት» ማለት የዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 በሚደነግገው መሠረት ማዘጋጃ ቤት በሚያስተዳድረው ክልል ውስጥ ተመርጠ የተሰየመና የተቋቋመ ም/ቤት ነው።
7. «ከተማ» ማለት በክልሉ ውስጥ ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመበት ወይም ቢሮው ከተማ ብሎ የሰየመው አካባቢ ነው።
8. «ኪንቲባ» ማለት የዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 4 በሚደነግገው መሠረት በምክር ቤቱ የሚመረጥ /የምትመረጥ/ የከተማው ህዝብ ተወካይ ነው/ናት/።

3. የተፈጻሚነት ወሰን

1. ይህ አዋጅ ቀደም ብለው በተደራጁትም ሆነ ወደፊት በሚቋቋሙት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ማዘጋጃ ቤቶች ተፈጻሚነት ይኖረዋል።
2. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተቋቋሙት ማዘጋጃ ቤቶች በመንግሥት የተሰጣቸው እውቅና እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ ህግ መሠረት እንደገና ይደራጃሉ።
3. የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ቢሮ በሚያቀርበው አስተያየት መሠረት ይህ አዋጅ የሚሆንባቸውን ከተሞች

implement a comprehensive municipal law which takes full advantage of the existing constitutional climate;

NOW, THEREFORE, in accordance with art. 49/3.1 of the constitution of the Amhara National Regional State which empowers the Regional Council to issue laws, it is hereby proclaimed as follows.

Chapter One
General

1. Short Title

This proclamation may be cited as: "The Municipalities Proclamation No 43/2000."

2. Definitions

In this proclamation, unless the context otherwise requires:

1. "Bureau" means the Bureau of Works and Urban Development of the Amhara National Regional State.
2. "City Manager" means the chief executive officer of a municipality appointed in accordance with article 12 hereof.
3. "Ministry" means The Ministry of Works and Urban Development.
4. "Municipal Cases" means cases over which municipal tribunals have exclusive jurisdiction as provided for under article 26 hereof.
5. "Municipality" means an entity established under article 4 hereof.
7. " Urban centre" means an entity established under article 4 here of.
8. "Mayor" means a representative of the city residents elected by the council in accordance with art.10 sub article 4 hereof

3. Scope of Application

1. This proclamation shall apply to all municipalities in the Amhara National Regional State as now or as established hereafter.
2. Municipalities established prior to the coming in to forth of this proclamation shall without prejudice to their municipal status sanctioned by the state be reorganized in accordance with the pertinent provisions of this proclamation.
3. The regional executive committee may on the recommendation of the Bureau determine the municipalities to which this proclamation would

322

322

~~229~~

ይወስናል። ስለአፈጻጸሙ ዝርዝር መመሪያ ይወጣል።

ምዕራፍ ሁለት
ስለማዘጋጃ ቤቶች በጠቅላላው

4. የማዘጋጃ ቤቶች ህጋዊ ሰውነት

በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የተቋቋመና ወደፊት የሚቋቋም በማናቸውም ደረጃ ላይ የሚገኝ ከተማ ነዋሪ ህዝብ የራሱ ህጋዊ ሰውነትና መጠሪያ ኖሮት በማዘጋጃ ቤትነት ይደራጃል። በዚሁ መጠሪያ አማካይነት ከሀገር ውስጥ ምንጮች የመበደር ስልጣንን ጨምሮ ማናቸውም ውል የመግባት፣ የንብረት ባለቤት የመሆንና የማስተዳደር፣ የመክሰስና የመከሰስ ህጋዊ ችሎታ ይኖረዋል።

5. የማዘጋጃ ቤቶች አላማዎች

1. የከተማውን ነዋሪ ህዝብ ፍላጐት መሠረት በማድረግ ተገቢ የሆኑ አገልግሎቶችን ማቅረብና የኑሮ ደረጃውን ማሻሻል፣
2. ውስጣዊ የአመራር ችሎታን በማጠናከር ተሳትፎንና በማበረታታት የራስ በራስ አስተዳደር መርሀን ተግባራዊነት በከተሞች ማረጋገጥ፣
3. ልዩ ልዩ የህብት ምንጮችን በማፈላለግ፣ በማስተባበርና ገቢን በማጐልበት፣ ከባቢያው ልማትን ማፋጠንና ለነዋሪው ህዝብ ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ እድገት አስተማማኝ መሠረት መጣል፣
4. ህብረተሰቡ በልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ፣ ከመንግሥትና አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በጐ ግንኙነት ፈጥሮ በመንቀሳቀስ አብሮ የመሥራት ባህልን ማዳበር፣
5. በከተሞች ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ኢንቨስትመንትን ማበረታታት።

6. ስለማዘጋጃ ቤቶች ሥልጣንና

1. በማናቸውም እርከን የተቋቋመ ማዘጋጃ ቤት በአማራ ብሔራዊ ክልል ህገ መንግሥትና በሌሎች ህጎች መሠረት ለእንድ ማዘጋጃ ቤት ህልውና የሚያስፈልጉት ሥልጣንና ኃላፊነቶች ሁሉ ይኖሩታል። ከዚህ በላይ የሠፈረው ድንጋጌ በህገ መንግሥቱና በሌሎች ህጎች የተሰጡትንና በዝሀሁ ህጎች በግልፅ ያልተከለከሉትን ሥልጣናት የሚያጠቃልል ይሆናል። ሁሉም ማዘጋጃ ቤቶች እኝህሁ ስልጣኖች በተሟላ ሁኔታ የሚኖራቸው ሲሆን በዚህ አዋጅ በግልፅ የተመለከቱት ዝርዝሮች በማናቸውም ሁኔታ የስልጣኑን መገደብ የሚያመለክቱ አይሆኑም፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የሰፈረው ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማዘጋጃ ቤቶች በተለይ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት

apply on progressive basis. Detailed guidelines shall be issued for the implementation of the same.

Chapter 2
Municipalities in General

4. Incorporation

The residents of an urban center of any grade as now established or as hereafter established in the manner provided by this proclamation shall constitute a municipal body corporate in perpetuity under the name born by that urban center and shall by virtue of such name have the legal capacity to enter into any contract, the capacity (to borrow from local sources included), own and manage property and sue and be sued.

5. Aims of Municipalities

1. avail appropriate services and improve standards of living in response to the needs and wishes of their residents;
2. ensure the exercise of democratic self-government by promoting internal leadership potential and encouraging self initiation;
3. Enhance local development and lay strong foundation for the sustainable economic growth of the residents by exploring, mobilising and co-ordinating various resources as well as raising the level of incomes.
4. Promote the active participation of the public in development activities and develop the spirit of co-operation by establishing a positive working relationship with the Government and other concerned bodies.
5. Encourage investment in urban centres by creating suitable environment

6. Powers and Responsibilities of Municipalities

1. A municipality of any grade shall have all the powers possible for a municipality to have under the constitution and other laws of the Amhara National Regional State. This includes all powers given by the constitution or other laws and all other powers not prohibited by such laws. The municipality shall have all such powers as fully and completely as though they were specifically enumerated in this proclamation; and no enumeration of powers herein shall be deemed exclusive or restrictive there of.
2. Without limiting the generality of the foregoing, municipalities may, inter alia, have the following powers and duties.

323

ይኖራቸዋል::

1. የአገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ

ሀ. አገር አቋራጭ ጎዳናዎችን ሳይጨምር የዋና ዋናና የመጋቢ መንገዶች ሥራ፣ የመንገድ መብራት አቅርቦትና የተፋሰስ ሥራዎች ዝግጅት፣ ከትራፊክ አገልግሎት ጋር የተያያዙ ሥራዎች፣ የአትክልት ቦታዎች፣ መናፈሻዎችና ክፍት የህዝብ መዝናኛ ሥፍራዎች ማደራጀት፣ የፍሳሽና የደርቅ ቆሻሻ አወጋገድና የጎርፍ ቁጥጥር አገልግሎት መስጠት፣

I) Regarding provision of services

A. The construction of roads and streets, [excepting inter-city roads], their lighting and drainage, provision of traffic services; establishment of gardens parks and public open spaces; provision of sewerage, refuse disposal and flood control services.

ለ.የማህበራዊ አገልግሎትን አቅርቦት በተመለከተ የመኖሪያ ቤቶችን አቅርቦት ማሻሻል፣ የቄራ አገልግሎት መስጠት፣ መናኸሪያዎችን ማደራጀት፣ የአንቡላንስ አገልግሎት ማደረጀት፣ የአፀደ ህጻናትና የጎልማሶች ትምህርት እንዲካሄድ ማድረግ፣ የማህበረሰቡን የአካባቢ መዝናኛ ማዕከላትና የመቃብር ሥፍራዎችን ማደራጀት::

B. Improvement of the supply of residential houses, the provision of abattoir services establishment of bus terminals, organization of ambulance services, the operation of nursery and adult education programs; establishment of community and local recreation centres as well as burial grounds.

ሐ.ማህበራዊ ዋስትናን በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋዊያን፣ ለወላጅ አልባና ከቤተሰብ ለተገለሉ ልጆች መርሃ ግብሮች እንዲቀረጹና እንዲፈጸሙ ማድረግ፣

C. As regards social security, in cooperation with concerned bodies, develop and execute programs for the care of the handicapped, the aged, the orphaned and abandoned children, in cooperation with the concerned bodies.

መ.ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የውሃ፣ አሌክትሪክ፣ የህዝብ ትራንስፖርትና የመሳሰሉት አገልግሎቶች አቅርቦት መሟላቱን ማረጋገጥ::

D. Ensure in cooperation with the concerned bodies, the provision of public utilities such as water, electricity and public transport in cooperation with the concerned bodies.

ሠ.እንደከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች፣ ሙዚየሞች፣ ቤተመጻሕፍትና የእሳት አደጋ መከላከያዎች ማቋቋም፣ ከሌሎች አካላት ጋር በመሆን የምግብና መጠጥ ቁጥጥር የማድረግ፣ የክብደትና መለኪያዎች ደረጃን ማረጋገጥ፣ እንዲሁም የብክለት ቁጥጥርና የመሳሰሉ የጠቃ አገልግሎቶችን መስጠት::

E. Provision of protective services such as establishing municipal tribunals, museums, public libraries and fire brigades and in collaboration with pertinent bodies carry out inspection of food and drinks, weights and measures and provide with pollution control and other similar services.

2. ማዘጋጃ ቤቱ በራሱ የማስፈፀም ኃላፊነት በማይወሰድባቸው እና በሰልጣኙ ሥር በማይወድቁ ጉዳዮች ላይ የማህበረሰቡን አባላት መወከልና ኃሳባቸውን መግለጽ፣

2) representing and voicing the opinion of the community on matters over which the municipality does not have executive responsibility;

3. በዚህ አዋጅና ወደፊት በሚወጣው ደንብ ተለይተው የሚገለጹትን ግብሮች፣ ቀረጦች፣ ክፍያዎችና ሌሎች የገቢ ምንጮችን መወሰንና መሰብሰብ፣

3) Levying and collection of taxes, charges, fees and other designated revenue sources; as maybe stipulated in this proclamation and regulation there under.

4. የፋይናንስ አጠቃቀምን በማሻሻል ብክነትንና ምዝበራን መቆጣጠር፣

4) control wastefulness and embezzlement by adopting improved financial systems,

5. የከተማ ልማትን ለማፋጠን እንዲቻል እንደ መንገድ ሥራ የመሳሰሉ የመሠረተ ልማት አቀርቦትን ማሻሻል፣ የልማት ማስፋፊያ ቦታዎች በወቅቱ ማዘጋጀትና በአግባቡ ለተጠቃሚዎች ማዳረስ

5) with the view to enhancing urban development, improve the provision of infrastructures such as road works and the percolation and allotment of development expansion sites;

ግዳሪስ

6.የከተማውን ፕላን እንዲዘጋጅ ማድረግ፣ ማፅደቅና ተፈጻሚነቱን ማረጋገጥ፣

7.የቦታ አገልግሎት አጠቃቀም ፕላንና የመሬት ካዳስተር ስርዓት በመዘርጋት ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ፣

8.የገቢያ ቦታዎች በማደራጀት፣ ንግድን በማስፋፋትና ደንን በማልማት እንደ ግብርና፣ ከብት እርባታ፣ አሣ ማስገርና አነስተኛ የጎጆ ኢንዱስትሪ ባሉት መስኮች ነዋሪው ህዝብ የምክር አገልግሎት የሚያገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

9.በህግና ሥርዓት አከባበር፣ በአካባቢ ጤና አጠባበቅና ጽዳት ደንቦች ተፈጻሚነት፣ ለመዝናኛና መጠጥ ቤት ሥራዎች ፈቃድ በመስጠት ረገድ ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት የሚደረግ እገዛንና ትብብርን ጨምሮ የቁጥጥር ተግባራትን ማከናወን፣

10.ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ከተሞች ጋር የእህትማማችነት ግንኙነት በመፍጠር የባህልና የቴክኖሎጂ ልውውጥ ማድረግ፣

3.ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው ቢኖርም የክልላዊ መንግሥቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከቢሮው ጋር በመመካከር አንድ ማዘጋጃ ቤት በአነስተኛ ሊፈጽማቸው የሚገቡ ተግባራትን ዝርዝር የያዘ ደንብ አውጥቶ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

7. የማዘጋጃ ቤትነት አቋም ስለማግኘት

1.የማዘጋጃ ቤት አቋም የላገኘ የማናቸውም ከተማ ነዋሪዎች ከተማቸው ይህው አቋም እንዲሰጠው ለቢሮው ሊያመለክቱ ይችላሉ።

2.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት የከተማ ነዋሪዎች ለቢሮው የሚያቀርቡት የማዘጋጃ ቤትነት አቋም መጠየቂያ ማመልከቻ በጽሁፍ ሆኖ የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ ይኖርበታል።

ሀ. የከተማውን ወሰን የሚያሳይ ካርታ

ለ. የከተማውን ነዋሪ ህዝብ ቁጥር

ሐ. የከተማውን የነፍስ ወዘፍ ገቢ

መ.ከተማው በአነስተኛ ሊፈፅማቸው የሚገቡትን ማዘጋጃ ቤት ነክ ተግባራት ለማከናወን ያለውን ድርጅታዊ ዝግጁነትና የገንዘብ አቅም

ሠ.ከመራጩ የከተማ ነዋሪ ህዝብ መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ጥያቄውን የደገፉት ስለመሆናቸው ማረጋገጫ የያዘ ሰነድ፣

3.ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ ሁለት ስር ያልተመለከቱ ሌሎች መመዘኛዎች አዋጁን ተከትሎ በሚወጣ ደንብ የሚገልፅ ይሆናል።

4.ቢሮው ነዋሪዎች ያቀረቡትን አቤቱታ ከተያያዘው

6) cause the preparation of municipal development plan, approve and there by ensure its enforcement;

7) develop an urban land use plan, devise a land information system and ensure its enforcement;

8.develop and ensure the enforcement of zoning and land information systems enhancing the economic development of the urban centre through the establishment of markets; the promotion of trade; a forestation; facilitating the provision of extension services to the public in such areas as agriculture, animal husbandry, fisheries, small scale industries;

9. carry out inspections including assistance provided to the concerned government bodies in the maintenance of law and order; enforcement of sanitation and hygiene regulations and licensing of entertainment and liquor trade,

10.Undertake cultural and technology exchange by creating sisterly relationships with cities at home and abroad.

3. Notwithstanding sub-articles 1 and 2 hereof, the executive committee of the Regional State may in consultation with the Bureau, issue regulations which define the minimum functions that a municipality shall perform

7. Acquisition of Municipal Status

1. The residents of an urban centre that has not acquired a municipal status may apply to the Bureau for such a status.

2. The application for municipal status that residents submit in accordance with sub-article 1 hereof shall be in writing and includes:

a. map showing the boundaries of the urban centre;
b. the population size of the urban center;
c. the per capita income of the urban center;
d. the organizational and financial capacity of the urban center to perform the minimum municipal functions;
e. a document which confirms that more than one-half of the voting population has endorsed the petition.

3. Other criteria not indicated under sub article 2 hereof shall be stipulated in a regulation to be issued pursuant to this proclamation

4. The Bureau shall, after considering the application

ማስረጃ ጋር በማዛመድ ከመረመረና ተቃውሞም ቢኖር ይህንኑ ተቀብሎ ካገናዘበ በኋላ በቀረበለት የማዘጋጃ ቤትነት አቋም ጥያቄ ላይ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ይሰጣል።

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ቢሮው በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማናቸውም ወገን ለክልሉ ም/ቤት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይግባኝ ማለት ይችላል። ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

8. ስለማዘጋጃ ቤቶች እርከን

1. ማዘጋጃ ቤቶች የከተማውን የነፍስ ወከፍ ገቢና ማኒስቴሩ ያወጣቸውን ሌሎች መስፈርቶች መሠረት በማድረግ በሚከተሉት 3 እርከኖች ይከፈላሉ፣

ሀ. እርከን 3 ማዘጋጃ ቤቶች
ለ. እርከን 2 ማዘጋጃ ቤቶች
ሐ. እርከን 1 ማዘጋጃ ቤቶች

2. እርከን 3 ከፍተኛውን የዕድገት ደረጃ ሲያመለክት፣ እርከን 1 ዝቅተኛውን የዕድገት ደረጃ ይወክላል።

3. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተመለከቱትን መስፈርቶች መሠረት በማድረግ ማዘጋጃ ቤቶችን በደረጃ ይመድባል።

4. ቢሮው በራሱ አነሳሽነትም ሆነ በሚመለከተው ማዘጋጃ ቤት ጥያቄ ተገቢ መስፈርቶች መሟላታቸውን አረጋግጦ የደረጃ ምደባውን እንደገና ሊያከናውን ይችላል።

ምዕራፍ ሶስት
ስለማዘጋጃ ቤቶች አደረጃጀት

9. ስለማዘጋጃ ቤቶች አካላት

1. ማናቸውም ማዘጋጃ ቤት የሚከተሉት አበይት አካላት ይኖሩታል፣

ሀ. የከተማ ም/ቤት
ለ. ቋሚ ኮሚቴ
ሐ. ከንቲባ
መ. የከተማ ሥራ አስኪያጅ /እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ሥራ አስኪያጅ/

2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም፣ ማናቸውም በእርከን አንድ ሥር የሚጠቃለል ከተማ ም/ቤት ራሱ እንደ ቋሚ ኮሚቴ ሆኖ በተጨማሪ ሊያገለግል ይችላል።

10. ስለከተማ ም/ቤት

1. ስለከተማ ምክር ቤት ሥልጣንና ኃላፊነት

ሀ. መላው የማዘጋጃ ቤት ስልጣን በዚህ አዋጅ መሠረት ለከተማ ም/ቤት ተሰጥቷል። ም/ቤቱም የማዘጋጃ ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት በአግባቡ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል።

ለ. ከዚህ በላይ በንዑስ ክፍል «ሀ» የተመለከተው ጠቅላላ ድንጋጌ ሳይነካ የከተማ ም/ቤት ከዚህ

along with the evidence submitted by the petitioning residents and receiving objections if any, decide within six months to grant or decline the prayer.

5. An aggrieved party may appeal from the decision of the Bureau to the Executive Committee of the Regional Council. The decision of the executive committee shall be final.

8. Grades of Municipalities

1. Municipalities may on the basis of per capita income of the city, and other criteria laid down by the Ministry, be classified into three categories:

a. Grade III municipalities
b. Grade II municipalities
c. Grade I municipalities

2. Grade III signifies a higher level of development whereas Grade I symbolizes a lower level of development.

3. The Bureau shall, on the basis of the criteria referred to under sub-article (1) hereof, categorize municipalities.

4. The Bureau may, at its own initiative or on application by a municipality recategorize such a municipality provided that the pertinent criteria have been fulfilled...

Chapter Three
Organization of Municipalities

9. Organs of Municipalities

1. A municipality shall have the following principal organs:

a) a municipal council
b) a standing committee
c) a mayor
d) a city manager (and a deputy manager where necessary.)

2. Notwithstanding the provision of sub-article 1 hereof, the municipal council of a Grade I urban center may use itself as the standing committee of the municipality.

10. The Municipal Council

1. Powers and Responsibilities of the Municipal Council

A. All powers of the municipality shall be vested in the municipal council; and the council shall provide for the exercise thereof and for the performance of all duties and obligations of the municipality.

B. Without affecting the generality of sub-section

በታች የተመለከቱት ልዩ ሥልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

1. ከሰልጣንና ኃላፊነታቸው ጋር የተዛመዱ ከባቢያዊ ፖሊሲዎችን ያወጣል፣ ዋና ዋና ውሳኔዎች ይሰጣል፣ እንዲሁም እነዚህኑ ለማስፈጸም የሚረዱ መመሪያዎች ያወጣል፣

2. የማዘጋጃ ቤቱን ድርጅታዊ መዋቅር ይወስናል። መምሪያዎችን፣ ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶችንና ሌሎች የሥራ ክፍሎችን አወቃቀር ያፀድቃል።

3. በየጊዜው የሚያወጣቸው ፖሊሲዎችና የሚሠጣቸው ውሳኔዎች በአግባቡ ተፈጻሚ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።

4. ከአባላቱ መካከል የማዘጋጃ ቤቱን ከንቲባ፣ የቋሚ ኮሚቴውን አባላትና ፀሐፊውን ይመርጣል።

5. የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶችን ፕሬዘዳንትና ዳኞች ይሾማል።

6. የከተማውን ሥራ አስኪያጅ ይሾማል። ደመወዙን፣ አበሉንና ሌሎች የሥራ ሁኔታዎችን ይወሰናል።

7. አስፈላጊ በሚሆንበት መጠን ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን፣ ቦርዶችንና ኮሚሽኖችን ያቋቁማል። ተግባራቸውንም ይወሰናል።

8. የከተማውን ፕላን ያፀድቃል፣ ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል።

9. የማዘጋጃ ቤቱ ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና ማስፈፀሚያ በጀት ረቂቅ መርምሮ ያፀድቃል። በአግባቡ መፈፀሙንም የረጋግጣል።

10. የማዘጋጃ ቤቱ የተመሠከረለት አዲተር በሚያቀርብለት ሪፖርት መሠረትም ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል።

11. አባላቱም ሆነ ለማዘጋጃ ቤቱ ተቀጣሪ ሠራተኞች የሚያገለግሉ የሥነ ምግባር መቆጣጠሪያ መመሪያ ያወጣል።

12. ለመራጩ ህዝብና አግባብ ላላቸው የመንግሥት አካላት ወቅታዊ ዘገባ ያቀርባል።

(a) hereof the municipal council shall have the following specific powers and responsibilities:

1. regarding matters falling under their jurisdiction make local policies, give major decisions and issue guidelines for the implementation of the same;

2. determine the organizational structure of the municipality, approve the establishment of line departments, support services and other offices;

3. follow up and supervise the proper implementation of its policies and decisions;

4. elect from among its members, the mayor, the secretary and members of the standing committee;

5. appoint the president and judges of municipal tribunals;

6. appoint the city manager and determine his or her salary, allowances and other working conditions;

7. establish committees, boards and commissions as deemed necessary; define their functions;

8. approve the city's plan and ensure its implementation;

9. approve the annual work programme and budget of the municipality and ensure the proper execution thereof;

10. appoint an accredited auditor for the municipality and there by render appropriate decisions on his report;

11. set standards of conduct for its members and the employees of the municipal authority;

12. report periodically to the electorate and to the pertinent state organ.

2. ስለ ምክር ቤት አባላት ምርጫና የአገልግሎት ዘመን

2. Election of members, Tenure of Office

ሀ. በእያንዳንዱ ማዘጋጃ ቤት ከተማ ነዋሪ ህዝብ ነጻ፣ ቀጥተኛ፣ ትክክለኛና ሚስጢራዊ የድምፅ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት ለአምስት ዓመታት የሚመረጡ ጎደሎ ቁጥር አባላት የሚኖሩት የከተማ ም/ቤት ይቋቋማል።

a. In every municipality, there shall be established a municipal council composed of odd number members elected by the voters of the urban center in a free, direct, equal and secret election for a period of 5 years.

ለ. የከተማ ም/ቤት አባላት ቁጥር አንድ የከተማ ክልል በውስጡ በሚይዛቸው የምርጫ ወረዳዎች ቁጥር የሚወሰን ይሆናል።

b. The number of voting districts within the municipal area shall determine the size of membership of a municipal council.

ሐ. ከዚህ በታች የተመለከተው ገደብ እንደተጠበቀ

c. Subject to the limitations hereunder, the number of

327

327

ሆኖ፣ እያንዳንዱ የምርጫ ወረዳ ባለው የህዝብ ቁጥር መሠረት ጭማታቸው የሚወሰን ተወካዮች ይኖሩታል። ሆኖም የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር ከ11 ሊያንስ ወይም ከ61 ሊበልጥ አይችልም።

መ/የምርጫ ወረዳዎች ቁጥር የሚመረጡትን የም/ቤት አባላት በሙሉ ቁጥር ላይ የሚያሳርፈው ወይም ያንኑ ቁጥር ከተደነገገው ቁጥር በታች ወይም በላይ የሚያደርገው ሆኖ ሲገኝ ም/ቤቱ አስፈላጊውን ማስተካከያ የሚደረግበትን አግባብ ይወሰናል። ሆኖም ማናቸውም ምክር ቤት በመጀመሪያ ጊዜ በሚቋቋምበት ወቅት በዚህ አዋጅ መሠረት ምክር ቤቱ የሚጠራለት የመንግሥት አካል አስቀድሞ የምክር ቤቱን አባላት ቁጥር ይወሰናል።

ሠ.የከተማ ም/ቤት አባላት መደበኛ ምርጫ በየአምስተ ዓመቱ ግንቦት ወር ላይ ይከናወናል፣

ረ.የማዘጋጃ ቤቶች ም/ቤቶች ምርጫ በምርጫ ህግ መሠረት ይፈጸማል፣

ሰ.ስለ ምክር ቤት አባላት ተዋጽኦና ብቃት ሁኔታ ዝርዝሩ ወደፊት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

3. ስለከተማ ከንቲባ

ሀ.የከተማ ም/ቤት በምክር ቤቱ በጎ ፈቃድ የሚያገለግለውን ከንቲባ ከአባላቱ መካከል መርጦ ይሰይማል።

ለ.የከተማው ም/ቤት የማዘጋጃ ቤቱን ሥራ ውስብስብነት መሠረት በማድረግ ከንቲባው በቋሚነት ወይም በትርፍ ሰዓት ግገልገል ያለበት ስለመሆኑ ይወሰናል።

ሐ.ከንቲባው የሚኮተሉት ሥልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

1. የም/ቤቱንና የቋሚ ኮሚቴዎችን ስብሰባዎች በሊቀመንበርነት ይመራል።
2. በመንግሥታዊ የሥራ ግንኙነቶች ረገድ ማዘጋጃ ቤቱን ይወክላል
3. በአፈሲላዊ ፕሮግራሞችና ዝግጅቶች ሁሉ የከተማው ርዕሰ መስተዳድርና አምሳባሳደር ሆኖ ይሠራል።
4. በም/ቤቱና በማዘጋጃ ቤቱ ሥራ አመራር መካከል በጎ የሥራ ግንኙነት እንዲኖር ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል።
5. የማዘጋጃ ቤቱን ሥራ አመራር ይቆጣጠራል፣ አፈጻጸሙንም እየገመገመ በ3 ወር አንድ ጊዜ ለከተማው ም/ቤት ዘገባ ያቀርባል።
6. ከከተማው ሥራ አስኪያጅ ጋር በመመካከር የማዘጋጃ ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴዎች ዘገባ የሚቀርብባቸውንና የነዋሪው ህዝብ አስተያየት የሚሰበሰባቸውን ህዝባዊ

representatives of each voting district shall be determined by the size of its population provided that the size of council membership shall neither be neither smaller than eleven (11) nor bigger than sixty-one (61).

d. Where the number of the voting districts is such as to make the number of council members even or to make the number below or above the prescribed size, the council shall determine the manner by which the necessary adjustments would be made; provided however that the membership size of any council to be established for the first time shall be determined by the Government body to which the council is accountable in accordance with this Proclamation.

e. The regular election of municipal council members shall be held once every five (5) years in the month of Genbot (May)

f. Municipal council election shall be conducted in accordance with the National Electoral Law.

g. The composition and qualification of council members shall be determined in the forthcoming regulation

3. The mayor

a. The municipal council shall elect from among its members a mayor who shall serve at the pleasure of the council;

b. The municipal council shall, depending on the complexity of the municipal work, determine whether the mayor should serve on a full-time or part-time basis;

c. The mayor shall have the following powers and responsibilities

1. preside over the meetings of the council and the standing committee;
2. represent the municipality in intergovernmental relationships;
3. act as the ambassador and head of the municipal government for all official programs and occasions;
4. facilitate a good working relationship between the council and the municipal management;
5. monitor and evaluate the city management and report thereon to the council once every three (3) months;
6. organize in consultation with the city manager, organize public forums where reports on municipal activities would be presented and the views of the public heard;

መድረክች ያዘጋጃል።

7.ከተማው ስለሚኖርበት ሁኔታ አመታዊ ንግግር ያደርጋል።

8.ለም/ቤቱ የሚሰጡትን ለሎች ተግባራት ያከናውናል።

መ.ከንቲባው በቋሚነት የሚያገለግል ከሆነ በምክር ቤቱ የሚወሰን ወርሀዊ ደሞዝና አበል ይከፈለዋል።

4. የምክር ቤቱ የአሠራር ሥነ ሥርዓት

ሀ. ም/ቤቱ በ3 ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል። ሆኖም በማዘጋጃ ቤቱ ከንቲባ ጥሪ ወይም ከአባላቱ መካከል 1/3ኛው ጥያቄ ካቀረቡ የም/ቤቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

ለ.ከም/ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሆኑት ከተገኙ የሰብሰባው ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል።

ሐ.ምልዓተ ጉባዔውን ካቋቋሙት አባላት መካከል የብዙሃኑን አብላጫ ድምፅ ያገኘ ማናቸውም ጉዳይ የም/ቤቱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል። ሆኖም የአባላት ድምፅ በእኩል ከተከፈለ ከንቲባው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

መ.የምክር ቤቱ ስብሰባዎች ሁሉ የሚካሄዱት በግልፅ ይሆናል። ሆኖም የክባቢያዊ ደህንነት ሁኔታ የህዝብ ሞራል ወይም የሦስተኛ ወገኖች መብት አደጋ ላይ የሚወድቅ ሲሆን የምቤቱ ስብሰባዎች በዝግ እንዲካሄዱ ሊወሰን ይቻላል።

ሠ.የምክር ቤቱ የሰብሰባ ቃለ ጉባኤዎች በመዝገብ እንዲያዙ ያደርጋል። መዝገቡም ለህዝብ ክፍት ይሆናል።

5. ስለ ከተማ ምክር ቤት መበተን

1.የሚመለከተው ከተማ ነዋሪ ህዝብ አስቀድሞ በሁኔታው ላይ ሳይወሰን አንድን የከተማ ምክር ቤት መበተን አይቻልም።

2.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ መንግሥት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የህዝቡን ጥቅም የሚጎዳ ከባድ ጥፋት መፈፀሙን ሲረዳው የከተማው ምክር ቤት ከሥራ አግዶ የማቆየትና ጉዳዩን የማጣራት ሥልጣን ይኖረዋል። ሥራውንም የሚመራ ጊዜያዊ የከተማ አስተዳደር ይሠይማል።

3.የክልሉ ምክር ቤት በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ተጣርቶ በቀረበለት ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል።

4.ውሳኔው የከተማውን ምክር ቤት እስከ መበተን የሚያደርስ ሆኖ ሲገኝ ከ6 ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አዲሱ የከተማ ምክር ቤተ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል።

7. deliver an annual state of the city address;

8. carry out such other functions as may be assigned to him by the council;

b) The mayor where permanently employed shall receive a monthly salary and allowance to be determined by the council.

4.Municipal Council Working Procedure

a. The council shall hold its regular meetings once in 3 months; provided that extraordinary meetings may be called by the mayor or at the request of one-third of the council members.

b. The presence of fifty percent plus one members of the council shall constitute a quorum.

c. Decisions of the council shall be taken by a majority vote of those members who constituted the quorum. In the event of a tie, the mayor shall have a casting vote;

d.All council meetings shall be public; provided however, that the council may decide to hold its meetings in camera where considerations of local security, public morale or the rights of others so require;

e. The council shall provide for the keeping of a journal of its proceedings. The journal shall be public.

5. Disbandment of the City council

1. No city Council shall be disbanded without the prior decision of the residents of the urban center concerned,

2. Not withstanding the stipulation of Sub-article 1 hereof, where the Executive Committees of the Regional Council is convinced that a grave act that is prejudicial to public interest has been committed, it shall have the authority to suspend the municipal council and conduct investigation. In such a case, it shall install a provisional administrative body which would direct the municipal functions,

3. The Regional council shall deliver a final decision on the basis of the findings of the Executive Committee,

4. Where the decision is to disband the municipal council, election for the new municipal council shall be held within a maximum period of six months

329

329

6. ክልከላዎች

ሀ. በሌላ ኃላፊነት ላይ ስለመመደብ

1.በህግ በተለይ ካልተፈቀደለት በስተቀር ማናቸውም የከተማ ም/ቤት አባል ተመርጠ አገልግሎት በሚሰጥበት ዘመን በምርጫ በሚያዝ ሌላ የህዝበ አገልግሎት ሥራ ሊሠማራ አይችልም::

2.ማንኛውም የከተማ ም/ቤት አባል ተመርጠ አገልግሎት በሚሰጥበት ዘመን በማዘጋጃ ቤቱ ውስጥ በሌላ ኃላፊነት ላይ ሊመደብ ወይም ተቀጥሮ ሊሰራ አይችልም::

3.ማንኛውም የከተማ ም/ቤት አባል ሆኖ ያገለገለ ማናቸውም ሰው ሥልጣኑን ከለቀቀበት ጊዜ ጀምሮ አንድ ዓመት እስኪሞላው ድረስ አስቀድሞ ባገለገለበት ማዘጋጃ ቤት ውስጥ ማካካሻ በሚከፈልበት ኃላፊነት ላይ በሹመት ሊመደብ ወይም ተቀጥሮ ሊሰራ አይችልም::

ለ. ስለ ቅጥርና ከሥራ ስለመገለል

ምክር ቤቱ ወይም ማናቸውም የምክር ቤቱ አባል የማዘጋጃ ቤቱ ሥራ አስኪያጅ በስልጣኑ የሚቀጥረውን የበታች ሠራተኛ አቀጣጠር ወይም አወጋገድ ጥያቄ በሚመለከት ጣልቃ እንዳይገባ የተከለከለ ሲሆን ሰለ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ማብራሪያ ከመጠየቅ ግን በዚህ ድንጋጌ አይታገድም::

ሐ. ለተፈላጊ ምርመራዎችና ፍተሻዎች ካልሆነ በስተቀር ምክር ቤቱም ሆነ የምክር ቤቱ አባላት ከማዘጋጃ ቤቱ ሹማምንትና ቅጥር ሠራተኞች ጋር አስተዳደራዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ የሚኖራቸው ግንኙነት በሥራ አስኪያጁ አማካኝነት ብቻ ይሆናል::

11. ስለከተማው ም/ቤት ቋሚ ኮሚቴ

1.በእርከን ሶስትና ሁለት ሥር በታቀፉ ማዘጋጃ ቤቶች ራሳቸውን በቋሚ ኮሚቴነት ተክተው የማገልገል አማራጭ ይኖራቸዋል::

2. በእርከን አንድ ሥር በታቀፈ ማዘጋጃ ቤቶች ያሉት ም/ቤቶች ራሳቸውን በቋሚ ኮሚቴነት ተክተው የማገልገል አማራጭ ይኖራቸዋል::

3.በማናቸውም ደረጃ የተቋቋመ ቋሚ ኮሚቴ ም/ቤቱ ከአባላቱ መካከል መርጦ በሚሰይማቸው ከንቲባውን ሳይጨምር ከ4-10 የሚደርሱ አባላት ይኖሩታል::

4.ቋሚ ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል::

ሀ.በም/ቤቱ ታይተው ውሳኔ የሚሰጥባቸውን የፖሊሲ ኃሳቦችን እያጠና ረቂቆችን ነድፎ ያቀርባል::

ለ.በምክር ቤቱ የወጡ ፖሊሲዎችና የተላለፉ ዋና ዋና ውሳኔዎች እንዲሁም ወቅታዊ

6.Prohibitions

a. Holding Other Office

1.Except where authorized by law, no council member shall hold any other elected public office during the term for which the member was elected to the council.

2. No council member shall hold any other office or employment within the municipality he serves during the term for which he was elected to the council.

3.No former council member may hold any compensated appointive office or employment with the city until one year after the expiration of the term for which the member was elected to the council.

B. Employments and Removals

Neither the city council nor any of its members shall interfere in matters relating to the employment or removal of any subordinate whom the city manager is empowered to employ; provided however, that, this provision may in no way bar the same from asking a pertinent body for necessary clarification.

c. Non-interference in Administration Except for purposes of necessary inquires and examinations, the council or its members shall deal with city officers and employees solely through the city manager.

11.The Standing Committee of the Municipal Council

1.There shall be established a standing committee of the municipal council in Grade III and Grade II municipalities.

2. Municipal councils in Grade I municipalities shall have the option of substituting themselves for the standing committee.

3. A standing committee shall be composed of the mayor and 4-10 members elected by the council from among its members.

4.The standing committee shall have the following duties and responsibilities:

a)study, formulate, and submit policy proposals for consideration by the council;

b) Follow up and monitor policies issued and carry out proper implementation of other decisions and

ዮና ዮና ውሳኔዎች እንዲሁም ወቅታዊ እቅዶች በአገባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ይገመግማል ውጤቱንም ለምክር ቤቱ ያቀርባል።

ሐ.በሥራ አስኪያጁ ተዘጋጅቶ የቀረበለትን የግዚጋጃ ቤቱን ዓመታዊ በጀት ረቂቅ መርምሮ ከአስተያየት ጋር ለምክቤቱ ያቀርባል።

መ.በግዚጋጃ ቤቱ ሥራ አስኪያጅ አሿሿምና ስንብት ረገድ ለምክቤቱ ኃላብ ያቀርባል።

ሠ.በግዚጋጃ ቤቱ ስም ተንቀሳቃሽ የባንክ ሂሣብ እንዲከፈት ፈቃድ ይሰጣል። ሂሣቡን በፊርማቸው የሚያንቀሳቅሱትን ይሠይማል።

ረ. በምክቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

5. ቋሚ ኮሚቴው የእለት ከእለት በሆኑ መደበኛ ሥራዎች ላይ የአስፈጻሚነት ሥልጣን አይኖረውም

6. የቋሚ ኮሚቴው የአሠራር ሥነ ሥርዓት

ሀ.ቋሚ ኮሚቴው በየ15 ቀኑ መደበኛ ስብሰባና በከንቲባው አነሳሽነት ወይም አንድ ሶስተኛ የኮሚቴ አባላት ሲጠይቁ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

ለ.አብዛኛው የኮሚቴ አባላት /50%+1/ በስብሰባው ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።

ሐ.ምልዓተ ጉባዔውን ካቋቋሙት አባላት መከከል የብዙሃኑን አብላጫ ድምፅ ያገኘ ማናቸውም ጉዳይ የኮሚቴው ውሳኔ ሆኖ ያልፋል። ሆኖም የአባላት ድምፅ በእኩል ከተከፈለ ከንቲባው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

12. ስለከተማው ሥራ አስኪያጅ

1.ማናቸውም ግዚጋጃ ቤት በሙያው በሰለጠነ የከተማ ሥራ አስኪያጅ ይመራል።

2.ስለሥራ አስኪያጅ ሹመት፣ ብቃትና ክፍያ ሁኔታ

ሀ.የከተማው ምክቤት በአብላጫ ድምፅ በተደገፈ ውሳኔ ሥራ አስኪያጁን ይሾማል፣ ክፍያውንና ጥቅማቅሞቹን ይወስናል።

ለ.የሥራ አስኪያጁ ሹመት በሙያ፣ በዳበረ ልምድና በበጎ ሥነ ምግባር ላይ ብቻ የተመሠረተ ይሆናል።

ሐ.የከተማው ምክር ቤት በሥራ አስኪያጁ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከስልጣኑ ሊያነሳው ይችላል። ሥራ አስኪያጁ ከስልጣን የወረደባቸው ምክንያቶችም ይህንኑ ለማረጋገጥ በሚጻፍ የስንብት ደብዳቤ ላይ ይገለፅለታል።

3. የሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ኃላፊነቶች

የግዚጋጃ ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ

proper implementation of other decisions and periodic plans rendered by the council, evaluate the same and report on its findings.

c) Review the annual budget proposal for the municipality presented by the city manager and submit same to the council with its considered opinion.

d) Initiate proposals to the council on the appointment and dismissal of the city manager.

e. Authorize the opening of current bank accounts in the name of the municipality and designate signiatories of the same.

f. Carry out such other duties as may be assigned to it by the council.

5. The standing committee may not have any executive power over such matters as are constitute day to day and regular activities by their nature.

6. Standing Committee's Working Procedure

a) The standing committee shall hold regular meetings every 15 days; provided however that, extraordinary meetings may be called by the mayor or at the request of 1/3rd or more of the members of the committee.

b) The presence of fifty percent and one of the committee members shall constitute a quorum.

c) Decisions shall be taken by a majority vote of those who constituted the quorum. In the event of a tie, the mayor shall have a casting vote.

12. **The City Manager**

1.Every municipality shall be managed by a professional city manager.

2.Appointment, qualification, and remuneration of the manager.

a. The municipal council shall, by a decision supported by a majority vote of its membership appoint a city manager and determine his/her remuneration and benefits there of.

b. The city manager shall be appointed solely on the basis of his professional qualifications, accumulated experience and good integrity.

c. The municipal council may remove the city manager from office whenever it loses confidence in him. The reasons for such removal of the city manager from office shall be set forth in the letter of dismissal as curtaining the same.

3.Powers and Responsibilities of the City Manager

The city manager, being accountable to the

331

331

ለከተማው ምቤትና ለቋሚ ኮሚቴው ሆኖ፣ የከተማው ዋና አስፈጻሚ ሹም በመሆን ይሠራል። በዚህም መሠረት የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

ሀ.የግዘጋጃ ቤቱን ሠራተኞች እንደአስፈላጊነቱ ይቀጥራል፣ ከሥራ ያገዳል ወይም ያሰናብታል።

ለ.የግዘጋጃ ቤቱን መምሪያዎች፣ አገልግሎቶች፣ የሥራ ክፍሎችና ወኪሎች አደራጅቶ በም/ቤቱ ያፀድቃል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል።

ሐ.የምክር ቤቱንና የቋሚ ኮሚቴውን ስብሰባዎች ይከታተላል። በሚያካሂዷቸው ውይይቶችም ይሳተፋል።

መ.የፌደራሉና የክልል መንግሥታት ህጎች፣ የከተማው ም/ቤት በየጊዜው የሚያወጧቸው ፖሊሲዎች፣ ደንቦች መመሪያዎች እንዲሁም የሚሰጣቸው ውሳኔዎች በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።

ሠ.የከተማውን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና ማስፈጸሚያ በጀት ረቂቅ አዘጋጅቶ በም/ቤቱ ታየቶ ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ለቋሚ ኮሚቴው ያቀርባል።

ረ.ወቅታዊ የሥራ ክንውንና ገንዘብ ነክ ዘገባዎችን ለቋሚ ኮሚቴውና ለም/ቤቱ ያቀርባል፣ ነዋሪው ህዝብም በተመሳሳይ ይህንኑ እንዲያውቀው ያደርጋል።

ሰ.ምክር ቤቱ ወይም እንደሆኒታው ቋሚ ኮሚቴው ተፈላጊ ሆኖ ባገኘው መጠን ሲጠየቅ ለሱ ዘገባዎችን ይሰጣል።

ሸ.በግዘጋጃ ቤቱ ገንዘብ ነክ ሁኔታና፣ በከተማው የወደፊት ፍላጎቶች ላይ ምክር ቤቱም ሆነ ቋሚ ኮሚቴው የተሟላ መረጃ ይኖራቸው ዘንድ ያማክራል።

ቀ.የከተማውን ጉዳዮች በተመለከተ ለም/ቤቱ ሌሎች ሃሳቦችንና አስተያየቶችን ይሰጣል።

በ.ጤናማ ግንኙነትና በመደጋገፍ ላይ የተመሠረተ ዝምድና ይጠናከር ዘንድ ከማህበረሰቡ ጋር በጎና ወዳጃዊ ትስስር እንዲኖር ያደርጋል።

ተ.በምክር ቤቱ ወይም በቋሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

13. ስለከተማው ምክትል ሥራ አስኪያጅ

የከተማው ምክትል ሥራ አስኪያጅ በምክር ቤቱ የሚሾምና ተጠሪነቱ ለሥራ አስኪያጁ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1.በሥራ አስኪያጅ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

2. ሥራ አስኪያጁ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ወቅት እርሱን ተክቶ ይሠራል።

municipal council and the standing committee, shall be the chief executive officer of the city. In that capacity he shall:

a. employ, suspend or remove all city employees,

b. establish and summit for approval by the council, direct and supervise line departments, support services, offices and agencies of the municipality.

c. attend all council and standing committee meetings and take part in their deliberations;

d. ensure the proper enforcement of the federal and state laws and implementation of policies, regulations, directives and decisions as may regularly be issued and rendered by the municipal council;

e. prepare and submit the annual work programme and budget proposal to the standing committee for council consideration and its subsequent decision;

f) submit periodic activity and financial reports to the standing committee and the council and make same available to the public;

g. avail such other reports as the council or the standing committee may require same;

h. Keep the city council and the standing committee fully advised as to the financial condition and the future needs of the city.

i. make other recommendations and opinions to the city council concerning the affairs of the city;

j. Maintain good and friendly ties with the community so as to strength healthy communication and supportive relationship.

k. Carry out such other duties as the council or the standing committee may assign him.

13. Deputy City Manager

The deputy City Manager, being appointed by the council and accountable to the city manager, shall have the following powers and responsibilities:

1. Carry out tasks specifically assigned to him by the city manager.

2. Act on behalf of the city manager in the absence of the later or where he is unable to perform his

14.ስለማዘጋጃ ቤት መመሪያዎችና የሥራ ክፍሎች

1.የከተማው ሥራ አስኪያጅ እንደአስፈላጊነቱ በሥሩ መምሪያዎች፣ ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶችንና ሌሎች የሥራ ክፍሎችን በማቋቋም ያፀድቃል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱት መምሪያዎች ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶችና ሌሎች የሥራ ክፍሎች ውስጣዊ አደረጃጀትና የሚሠሩባቸው ደንቦች ዝርዝር በሥራ አስኪያጁ ተዘጋጅቶና ለከተማው ም/ቤት ቀርቦ ወደፊት በማፀድቅ አስተዳደራዊ መመሪያ ይደነገጋል።

3. ሥራ አስኪያጁ ለርሱ ተጠሪ የሆኑ የማዘጋጃ ቤቱ መምሪያዎች፣ ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶችና ሌሎች የሥራ ክፍሎችን የሚመሩ ኃላፊዎችን መርጦ በም/ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ ይሾማል። ይህንኑ ሥርዓት ተከትሎም ከኃላፊነታቸው እንዲሰናበቱ ያደርጋል።

ምዕራፍ አራት
ስለግንኙነቶች

15. ከመንግሥት ጋር ስለሚኖሩ ግንኙነቶች

1.ማናቸውም ማዘጋጃ ቤት በተቋቋመበት የከተማ ክልል ውስጥ ከሚንቀሳቀሱ የክልልና የፌዴራል መንግሥታት ወይም እነርሱ ከሚቆጣጠሯቸው መምሪያዎች ወይም ወኪሎች ጋር በጋራ ወይም በትብብር፣ በውል ወይም በለጋሳ ሁኔታ፣ ሽርክና ገብቶ በመሥራት በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን ሥራ ላይ ሊያውል ወይም ተግባራቱን ሊፈፅምና በመዋዕለ ንዋይ አትርቦት ሙምር ሊሣተፍ ይችላል።

2. ማናቸውም ማዘጋጃ ቤት ከክልሉ መንግሥት ጋር በሚደረግ ስምምነት አቅሙና ችሎታው በሚፈቅድለት መጠን መንግሥታዊ ተግባራትን ያከናውናል። እንደዚህ ባለው አጋጣሚ ሁሉ ሥራዎችን በተገቢ ሁኔታ ለመፈጸም የሚጠይቀውን ፈንድና ቁሳቁስ መንግሥት ለሚመለከተው ማዘጋጃ ቤት የማቅረብ ኃላፊነት ይኖርበታል።

3. በአማራ ብሔራዊ ክልል ህገ መንግሥት አንቀጽ 86 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በከተማ ክልል ውስጥ የሚቋቋሙ ቀበሌዎችና ሌሎች መሰል አስተዳደራዊ ክፍሎች ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለመራጩ ህዝብና ለታቀፉበት ማዘጋጃ ቤት ይሆናል።

4. በአሁኑ ወቅት እየተሠራበት ካለው የቀበሌ ወረዳ ግንኙነት ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ ሥር ወደ ተገለፀው አወቃቀር የሚደረገው ሽግግር በዚህ አዋጅ በምዕራፍ አሥራ አንድ

duties.

14. Municipal Departments and Offices

1. The city manager may establish and submit for approval line departments, support services and other offices as are deemed necessary.

2. The internal organization of the departments, services and offices referred to under sub-article 1 hereof and the rules and regulations governing their operations shall be stipulated in an administrative guideline to be prepared by the city manager and approved by the municipal council.

3. The city manager shall nominate and submit for appointment by the standing Committee proposed heads of departments, support services and other offices that are directly accountable to him. He shall also relieve them of their duties following the same procedure.

Chapter Four
Relations

15. Intergovernmental Relations

1.The municipality may exercise any of its powers or perform any of its functions and may participate in the financing thereof, jointly or in cooperation, by contract or otherwise with the Regional or Federal governments or with any of their departments or agencies operating within the boundaries of the municipal area.

2. Any municipality may, by an arrangement with the Regional state, carry out state functions that its capacity warrants. In such instances, the state shall make available to the said municipality funds and facilities that the proper performance of the functions requires.

3. Without prejudice to the provisions of article 86 of the constitution of the Amhara National Regional State, Kebeles and other similar administrative units as hereafter established within the boundaries of an urban center shall be directly accountable to the electorate and the municipal administrations comprising them.

4. The transition from the existing Kebkele-Woreda arrangement currently in force to that arrangement stipulated under sub-article 3 hereof shall be as provided under chapter 11 hereof

በተደነገገው መሠረት ይፈጸማል።

5. ስለ ተጠሪነት

ሀ.በእርከን ሁለትና አንድ ሥር የታቀፉት ማዘጋጃ ቤቶች ተጠሪነታቸው ለመራጩ ህዝብና በመሰኑ ለሚጠቃለሉበት ወረዳ መስተዳድር ይሆናል።

ለ.ከዚህ በላይ በንዑስ ክፍል ሀ የተደነገገው ቢኖርም በእርከን ሁለት የታቀፉ ማዘጋጃ ቤቶች ይህ አዋጅ በወጣበት ወቅት የከተማ ወረዳ ምክር ቤት የነበራቸው ወይም የዞን ማዕከል መሆናቸው ከታወቀ በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 77 እና 79 በተደነገገው መሠረት የወረዳው ልዩ መብትና ጥቅም እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪነታቸው ለመራጩ ህዝብና ለሚመለከታቸው የዞን መስተዳድሮች ይሆናል።

ሐ.በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 77 በተደነገገው መሠረት የሚመለከተው ወረዳ ልዩ መብትና ጥቅም እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በእርከን ሶስት የታቀፉ ማዘጋጃ ቤቶች ተጠሪነታቸው ለመራጩ ህዝብና ለሚመለከታቸው ዞኖች ይሆናል።

መ.በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 69 /7፣8/ ባህር ዳርን በልዩ ዞን አስተዳደር ለማደራጀት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ርዕስ ከተማ የሆነችው ባህር ዳር የራሷ የከተማ ጉዳዮችን የሚያስተናግድ የከተማ ምክር ቤት ይኖራታል። ተጠሪነቱም ለመራጩ ህዝብና ለክልሉ ምክር ቤት ይሆናል።

ሠ.ከላይ በንዑስ ክፍል ከሀ-መ የተደነገገው ቢኖርም የከተሞች የወደፊት እድገት እየታየ ተጠሪነታቸው እንደአስፈላጊነቱ ሊሻሻል ይችላል።

16. ከነዋሪው ህዝብ ጋር ስለሚኖር ግንኙነት

1.የማዘጋጃ ቤት አካላት ተረክበው የሚሠሩበት ሥልጣን ሁሉ፣ ምንጩ የከተማው ነዋሪ ህዝብ ነው። የሥልጣን ባለቤት ማህበረሰቡ ነው።

2.የከተማ ነዋሪዎች የማዘጋጃ ቤትም ሆነ የቀበሌ ም/ቤቶች አባላትን መርጠው የመሰየምና ኃላፊነታቸውን በተገቢው መንገድ መወጣት ባልቻሉበት ጊዜ ሁሉ ደግሞ ከስልጣናቸው የማንሳት መብት አላቸው።

3.ማናቸውም የከተማ ም/ቤት፣ ህዝቡ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግል ባለሃብቶች በውሳኔ አሰጣጥና አፈጻጸም ሂደት ነትተው እንዲሳተፉ ያበረታታል። ለዚሁም እንዲያመች የከተማ ጉዳዮችን በሚመለከት ረገድ አስፈላጊውን መረጃ የመስጠት ግዴታ

5. Accountability:

a. Grade II and Grade I municipalities shall be accountable to the electorate and the respective Woreda administrations within the boundaries of which they are embraced.

b. Notwithstanding the provisions of Sub-section (a) hereof Grade II municipalities which, on the enactment of this Proclamation happened to have an urban Woreda Council or are equally the seats of administrative zones shall, without prejudice to the specific rights and entitlements of the woreda guaranteed by articles 77 and 79 of the Constitution, be accountable to their electorate and respective zonal administrations.

c. Without prejudice to the specific rights and entitlements of the woreda as provided for under article 77 of the Constitution, Grade III municipalities shall be accountable to the electorate and to their respective zonal administration.

d. Without prejudice to the provision of article 69 sub-article 7 and 8 of the Constitution stipulating for the organization of the city as a special zone, Bahir Dar, being the capital of the regional State shall have its own municipal council capable of handling its municipal affairs. The accountability of the council shall be to the electorate and the Regional Council.

e. Notwithstanding sub-sections a -d hereof, the accountability of urban centers may be changed from time to time depending on the level of development they will have accomplished.

16. Community Relations

a. All mandates bestowed upon and exercise by municipal organs emanates from the community. As such, the community is the source of all powers vested in municipalities

b. City residents shall have the right to elect members of the municipal and Kebele councils and recall them when they fail to discharge their responsibilities properly.

c. Any municipal council shall constantly inform the residents of the city, the NGO community and the private sector about municipal affairs with the view to encouraging their participation in the decision making and implementation process.

ይኖርበታል::

4. የከተማው ነዋሪዎች እንደበጀት፣ የድርጊት መርሃ ግብር፣ የሥራ ክንውን፣ ገንዘብ ነክ ዘገባዎች እና እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ የሚወያዩባቸውና አስተያየቱን የሚገልፁባቸው እንደጠቅላላ ስብሰባዎች፣ ህዝባዊ ውይይቶችና ክርክሮች ያሉ መደበኛ መድረኮች በም/ቤቱ ይደራጃሉ::

5. የከተማ ነክ ተግባራት ውጤታማ ተፈጻሚነት የነዚህን አካላት መቋቋም የሚጠይቅ ሆኖ ሲገኝ ም/ቤቱ የከተማ ነዋሪዎች በማዘጋጃ ቤቱ ሥር በሚዋቀሩ ቦርዶችና ኮሚቴዎች ገብተው ያገለግሉ ዘንድ ሊጋብዛቸው ይችላል::

6.በአንድ ማዘጋጃ ቤት ክልል ከሚኖረው መራጭ ህብረተሰብ ውስጥ ቁጥራቸው አስር ከመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ አባላት ለከተማውና ለነዋሪዎቹ አስፈላጊ ነው ብለው በሚያምኑበት ማናቸውም ጉዳይ ይመክርበት እና /ወይም/ ተገቢው ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ለም/ቤቱ የማመልከት መብት አላቸው::

ምዕራፍ 5
ስለ ማዘጋጃ ቤቶች በጀትና የፋይናንስ አስተዳደር

17. **የበጀት ዓመት**

ማናቸውም ማዘጋጃ ቤት የሚሠራበት የበጀት ዓመት የክልሉ መንግሥት የበጀት ዓመት ይሆናል::

18. **ስለበጀት**

1.ለተከታዩ የበጀት ዓመት የሚያገለግለው የማናቸውም ማዘጋጃ ቤት አመታዊ የበጀት ረቂቅ በከተማው ሥራ አስኪያጅ ተዘጋጅቶና በቋሚ ኮሚቴው ተመክሮበት በየዓመቱ ግንቦት 30 ቀን ወይም ከዚያ በፊት ለም/ቤቱ መቅረብ ይኖርበታል::

2.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው የበጀት ረቂቅ የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ ይኖርበታል::

ሀ. ታሳቢ አላማዎች፣ ተግባራትና ግቦች ለ.የታሰበው የካፒታልና የሥራ ማስኬጃ ወጪ ሐ. የሚጠበቀው ገቢና ምንጩ

3.ም/ቤቱ ይፋ የሆነ የበጀት ሰማ ካደረገና በጉዳዩ ላይ ውይይቶች ካካሄደ በኋላ በጀቱን ያፀድቃል:: በጀት የሚፀድቀው በየዓመቱ ሰኔ 30 ቀን ወይም ከዚያ በፊት ይሆናል::

4.ሁኔታዎች ባስገደዱ መጠን ም/ቤቱ የበጀት ማስተካከያዎችን ሊያደርግ ይችላል::

5.ማናቸውም ማዘጋጃ ቤት ከመንግሥት ያገኘውን ድጐማ ለታለመለት አገልግሎት ስለማዋሉ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በማረጋገጥ ሪፖርት ያቀርባል::

19. **ስለፋይናንስ አያያዝና አስተዳደር**

d. Regular forums such as general meetings, public discussions and debates shall be organized and executed by the council for the residents to discuss and express their views on such matters as budget, plan of action, performance and financial reports, and other items of similar nature.

e. The council shall invite city residents to serve on boards or committees whenever the effective performance of municipal functions requires the establishment of such bodies

f. Ten percent or more of the electorate of a municipality shall have the right to apply to the council to deliberate and/or decide on matters that they consider being important to the city and its residents.

Chapter Five
Municipal Budget and Financial Administration

17. **Fiscal Year**

The fiscal year of every municipality shall correspond with that of the Regional state.

18. **Budget**

1. The annual budget proposal for the ensuing fiscal year shall, after having been prepared by the city manager and debated by the standing committee be presented to the council on or before 30th of Ginbot each year

2. The budget proposal shall indicate the following particulars

   1. the envisaged objectives, tasks and goals;
   2. the proposed capital and revenue expenditure;
   3. the anticipated income and its sources;

3. The council shall after holding a public hearing and conducting deliberation adopts the budget. The budget shall be adopted on or before 30 Sene each year.

4. The council may make budgetary adjustments where circumstances so require.

5. Any municipality shall submit a report at the end of every fiscal year confirming that Government grant-in-aid has been utilized for the planned purpose.

19. **Management and administration of**

1.እያንዳንዱ ማዘጋጃ ቤት የራሱን ፋይናንስ የማደራጀትና የማስተዳደር ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል::

2.ማናቸውም ማዘጋጃ ቤት በዚህ አዋጅና በሌሎች ህጎች መሠረት ከልዩ ልዩ አርእስቶች የሚሰበስባቸው ገቢዎችና የሚቀበላቸው ክፍያዎች የሚከማቹበት የባንክ ሂሣብ በስሙ ይከፍታል:: ያንቀሳቅሳል::

3.ቢሮው አጥንቶ በሚያቀርበው መሠረት የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ማዘጋጃ ቤቶች የሚሠሩበትን የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ያወጣል::

20. ስለማዘጋጃ ቤቶች የገቢ ምንጮች

1. የከተማ ም/ቤቶች የህንጻ ታክስና የአፈር ኪራይን ጨምሮ ግብርና ቀረጥ የመጣልና የመሰብሰብ፣ እንዲሁም በህግ መሠረት የአገልግሎት ክፍያዎች ወስኖ የማስከፈል ሥልጣን ይኖራቸዋል::

2. የከተማ ም/ቤቶች ነዋሪ ህዝብ ሲፈቀድና የክልሉ መንግሥት ሲስማማ፣ እየተሠራበት ያለውን የክፍያ መጠን ከማሻሻል ጎን ለጎን አዳዲስ ግብር፣ ቀረጥና የአገልግሎቱ ክፍያዎች የመጣል ስልጣን ይኖራቸዋል:: ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል::

3. የከተማ ም/ቤቶች በፈቃደኝነት ከማሰበሰቡ መዋጮዎች፣ ስጦታዎችና የተፈቀዱ ድጎማዎች ፈንዶችን ያመነጫሉ::

4. የፌደራልና የክልል መንግሥታት ለማዘጋጃ ቤቶች አርዳታና ድጋፍ እርዳታ በልማት ረገድ ፍትሃዊነትን በሚያበረታታ፣ በጎ ተግባርን በሚያጠናክርና የተሳሳቱ አቅጣጫዎች በሚገታ፣ እንዲሁም ማዘጋጃ ቤቶች ያላቸውን ሃብት በሚገባ ጥቅም ላይ እንዲያውሉ ለማስቻል መንገድ የሚሠጥ ይሆናል::

5.ማዘጋጃ ቤቶች በህግ መሠረት አስቶክና ተዘዋዋሪ የዕዳ ሰነዶችን በመሸጥ ተጨማሪ ፈንድ ሊያመነጩ ይችላሉ::

6.ማናቸውም የከተማ ም/ቤት ከጠቅላላ አባላቱ መካከል ከግማሽ በላይ የሆኑት ሲስማሙ ለካፒታል ወጪዎች አላማ ከመንግሥት ወይም ከተመዘገቡ የፋይናንስ ተቋማት ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ገንዘብ ለመበደር ይችላል:: ሆኖም የትኛውም ማዘጋጃ ቤት ቢሆን በቅድሚያ የከተማውን ነዋሪ ህዝብ ስምምነት ሳያገኝ ከዓመታዊ ገቢው 10% ያለፈ የገንዘብ ብድር ቢጠይቅ ለማግኘት አይፈቀድለትም:: ዝርዝሩ ማዘጋጃ ቤቱ ወደፊት በሚያወጣው ገንዘብ ነክ የአፈጻጸም መመሪያ ይገለጻል::

21. ስለሂሣብ መዛግብትና ቁጥጥር

Finances

1.Every municipality shall have the power and responsibility to organize and manage its finance.

2.Each municipality shall open and operate a bank account into which shall be deposited all monies and revenues raised or received under this proclamation or other laws.

3. The regional executive committee shall on the basis of a study to be made by the Bureau issue financial management regulations for use by municipalities.

20. Revenue sources of municipalities

1. Municipal councils shall have the authority to levy and collect taxes and charges including building taxes and land rentals and set fees in accordance with the law.

2. Municipal councils shall have the authority to impose new taxes, charges and fees including adjustment of existing rates subject to approval by the residents and the council of the Regional state. Details shall be provided by regulations.

3. Municipal councils may raise funds from voluntary contributions, donations and authorized grants.

4. The Federal and the Regional State Governments may extend grants-in-aid to municipalities. Such assistance shall be extended with the view to encouraging equity in development; reinforcing good practice and discouraging wrong directions and spurring cities to exploit and make proper use of their resource.

5.Municipalities may raise additional funds through the sale of stocks and floating bonds in accordance with the law.

6. A municipal council may, by a majority vote of all its members, borrow in accordance with the law for purposes of capital expenditure either from the Government or registered financial institutions; provided however that no municipality may be permitted to obtain loan which exceeds 10% (ten percent) of its annual revenue without securing the prior consent of the city residents. Details shall be provided for in the financial guidelines to be issued by the municipality concerned.

21. Books of Accounts and Audit

1. ማናቸውም ማዘጋጃ ቤት ትክክለኛነታቸው የተረጋገጡና የተሟሉ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።

2. ማናቸውም ማዘጋጃ ቤት በየእለቱ የሚያከናውናቸው የሃብት አመዳደብና አጠቃቀም የተመለከቱ ሥራዎች አሰቀድሞ በፀደቀው የፋይናንስ አፈጻጸም ደንብ መሠረት መከናወናቸውን የሚያረጋግጥ የውስጥ አዲተር ይኖረዋል።

3. የከተማው ምክር ቤት የማዘጋጃ ቤቱን የሥራ ክንውን በየዓመቱ የሚገመግም፣ የከተማው ፈንድ በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋል አለመዋሉን የሚያጣራና በሥራ አስኪያጁ የሚቀርቡ ዘገባዎች ትክክለኛና ምሉዕነት ያላቸው ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የተመሠከረለት የውጭ አዲተር ይሰይማል።

1. Every municipality shall maintain accurate and complete books of accounts

2. Every municipality shall have an internal auditor who shall ensure that the daily resource management and utilization practices of the municipality have been effected in accordance with approved financial regulations.

3. The municipal council shall appoint an accredited external auditor who shall annually evaluate the performance of the municipality; check that municipal funds have been properly utilized and accounted for and that reports presented by the city manager are complete and accurate.

ምዕራፍ ስድስት
ስለሰው ኃይል አስተዳደር

Chapter Six
Personnel Administration

22. መሠረቱ

1. እያንዳንዱ ማዘጋጃ ቤት በማዘጋጃ ቤቶች የሰው ኃይል አስተዳደር ህግ መሠረት የራሱን ሠራተኛ የመቅጠር፣ የመመደብ፣ የማሳደግ፣ ደመወዝና ልዩ ልዩ አበሎቻቸውን የመወሰን፣ እንደአስፈላጊነቱ የሥነ ሥርዓት እርምጃ የመውሰድና ከሥራ የማሠናበት ስልጣን ይኖረዋል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ መሠረት የሚከናወነው የከተማ ሥራ አስኪያጅ ሹመት፣ የሠራተኞች ቅጥርና የደረጃ እድገት በአስተማማኝ ፈተና ወይም በሌላ የብቃት ማረጋገጫ በተደገፈ የተሟላው ወይም የተቀጣሪው የግል ችሎታና የሥራ ተስማሚነት ላይ ተመሥርቶ የሚፈፀም ይሆናል።

22. Principle

1. Every municipality shall have the authority to hire, post, promote, determine the salaries and allowances of, discipline and dismiss its staff in accordance with municipal personnel service laws to be studied and issued afterwards

2. All appointments, engagements, and promotions of city officers and employees shall be undertaken solely on the basis of personnel merit and fitness of the candidate demonstrated by a valid or reliable examination or other evidence of competence

23. ስለማዘጋጃ ቤቶች የሰው ኃይል አገልግሎት ቦርድ መቋቋም

1. የማዘጋጃ ቤቶች የሰው ኃይል አስተዳደር ህጎችን መንደፍ፣ ማሻሻል እና ተፈጻሚነታቸውን መቆጣጠርን፣ ማዘጋጃ ቤቶችን በሰው ኃይል አመራር መደገፍን፣ የሰው ኃይል አመራር ደረጃዎች ማሻሻልንና የብቃትና ችሎታ ማስከበሪያ ሥርዓት ተጠብቆ እንዲሠራበት መጣርን አለማዎቹ ያደረገ የማዘጋጃ ቤቶች የሰው ኃይል አገልግሎት ቦርድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተቋቋመው ቦርድ በዲሲፕሊን ጉዳዮች ላይ የግባኝ ሰሚ የዳኝነት አካል ሆኖ በተጨማሪ ሊያገለግል ይችላል። ዝርዝሩ ይህን አዋጅ መሠረት አድርጎ ወደፊት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

3. የማዘጋጃ ቤቶች የሰው ኃይል አገልግሎት

23. Establishment of Municipal Personnel Service Board

1. A Municipal Personnel Service Board is hereby established with its purposes being to formulate, develop and supervise the implementation of municipal personnel service laws, assist municipalities with personnel management, develop personnel management standards and help protect the merit system.

2. The Board shall further serve as a tribunal of appeal in disciplinary matters. Details shall be provided in a guideline to be issued pursuant this proclamation.

3. The composition of municipal Personnel Service

337

337

ቦርድ ከየእርከኑ የሚመለከታቸው ማዘጋጃ ቤቶችና መንግሥታዊ ተቋማት ተወጣጥቶ በክልሉ መንግሥት ይቋቋማል። ዝርዝር በህግ ይወሰናል።

4. የማዘጋጃ ቤቶች የሰው ኃይል አገልግሎት ቦርድ ተጠሪነቱ ለክልሉ ም/ቤት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይሆናል።
5. ቦርዱ እንደአስፈላጊነቱ የራሱን የሥራ ማከናወኛ ደንቦችና ሥነ ሥርዓቶችን ያወጣል።

ምዕራፍ ሰባት
ስለ ማዘጋጃ ቤቶች የዳኝነት ሰሚ አካል

24. ስለመቋቋም

የዚህ አዋጅ አንቀጽ 37 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው እያንዳንዱ ማዘጋጃ ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሁለት እርከኖች የሚያጠቃልል የከተማ ነክ ጉዳዮች ፍርድ ቤት ሊያቋቁም ይችላል።

1. የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት
2. ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት

25. ስለፍርድ ቤት አደረጃጀት

1. ፍርድ ቤቱ አንድ ፕሬዚደንት፣ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ዳኞችና ሌሎች ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ይኖሩታል።
2. የፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንትና ዳኞቹ በከንቲባው አቅራቢነት በከተማው ምክር ቤት ይሾማሉ።
3. ጉዳዩ የሚመለከተው ማዘጋጃ ቤት ፍላጎት በሚጠይቀውና አቅሙ በሚፈቅደው መጠን ብዛት ያላቸው ችሎቶች በፍ/ቤቱ ይደራጃሉ።
4. በእያንዳንዱ ችሎት አንድ ወይም ከዚያም በላይ ዳኛ ሊያስችል ይችላል።

26. ስለፍ/ቤቱ ሥልጣን

ፍ/ቤቱ ከሚከተሉት በሚመነጩ ወይም ከእነርሱ ጋር ተዘግጅነት ባላቸው ከተማ ነክ ጉዳዮች ሁሉ የተሟላ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል።

1. የከተማ ፕላንና የቦታ ምደባ ህግጋት አፈፃፀም
2. የቤቶችና የከተማ ቦታ አጠቃቀም
3. የማዘጋጃ ቤት ግብር፣ ቀረጥና የአገልግሎት ክፍያዎች
4. ጤናና የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ
5. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት
6. የትራፊክ ደንብ መተላለፍ ጉዳዮች

27. ተፈጻሚነት ስለሚኖራቸው ህጎች

1. ከዚህ በላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የክልሉን መንግሥት መደበኛ ፍ/ቤቶች የሚመለከቱ ህጎች ለከተማ ነክ ፍ/ቤቶች በተመሳሳይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

Board that is to consist of the representatives of the various grades of municipalities and government bodies shall be identified and designated by the regional Government. Details shall be provided by regulations.

4. The Municipal Personnel Service Board shall be accountable to the Executive Committee of the Regional council.
5. The Board may issue its own rules of working procedure as may be necessary.

Chapter Seven
Municipal Tribunal

24. Establishment

Subject to article 37 hereof, every municipality may establish a municipal tribunal having the following two tiers:

1. The tribunal of first instance
2. The appellate tribunal

25. Organization of the Tribunal

1. The tribunal shall have a president, the required number of judges and a support staff.
2. The president and the judges of the tribunal shall on the proposal of the mayor be appointed by the municipal council;
3. There shall be organized as many divisions of the tribunals as the need and the capacity of the municipality concerned may justify;
4. One or more judges may sit in every division.

26. Jurisdiction of the Tribunal

The Tribunal shall have exclusive jurisdiction over all municipal cases which arise from or are related to the following:

1. Implementation of urban planning and zoning laws.
2. housing and urban land use;
3. municipal taxes, charges and service fees;
4. protection of health and environmental sanitation;
5. municipal services.
6. cases of traffic violation.

27. Applicable Laws

1. Without prejudice to the foregoing provisions, all laws, which apply to regular courts and judges in the Regional state, shall mutatis mutandis apply to municipal tribunals.

338

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክተማ ነክ ፍ/ቤት ዳኞችን አስተዳደር የሚመለከት ደንብ ወደፊት በክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ወጥቶ በሥራ ላይ ይውላል።

ምዕራፍ ስምንት
ስለማህበራት

28. ስለማህበራቱ መቋቋም

1. ማዘጋጃ ቤቶች ማህበራትን የመመስረት፣ የማደራጀትና በእንቅስቃሴዎቻቸው ረገድ ንቁ ተሳትፎ የማድረግ መብት አላቸው።
2. ቁጥራቸው አምስት ወይም ከዚያ በላይ ሆኖ በአንድ ዞን መስተዳድር ውስጥ የሚገኙ ማዘጋጃ ቤቶች መሠረታዊ የማዘጋጃ ቤቶች ማህበር ሊመሠርቱ ይችላሉ።
3. በአንድ ዞን መስተዳድር ውስጥ የሚገኙ ማዘጋጃ ቤቶች ቁጥር ከአምስት ያነሰ ሆኖ ሲገኝ ከሌላ ዞኖች ጋር በጣምራ መሠረታዊ ማህበር ሊያቋቁሙ ይችላሉ።
4. በአንድ ዞንም ሆነ በጣምራ የተቋቋሙ መሠረታዊ ማህበራት በመዋሃድ ክልል አቀፍ የማዘጋጃ ቤቶች ማህበር ሊያቋቁሙ ይችላሉ።
5. የማዘጋጃ ቤቶች ማህበራት የየራሳቸው ህገ ማህበራት ሊኖራቸው ይችላል።

29. ስለምዝገባ

በዞን፣ በዞኖች ጣምራና በክልል አቀፍ ደረጃ የተቋቋሙ ማህበራት ጉዳዩ በሚመለከተው ሥራና ኮተማ ልማት ቢሮ እየቀረቡ ይመዘገባሉ።

30. ስለማህበራቱ ተግባራት

በዚህ ዝርዝር ያልተመለከቱ ሌሎች ተግባራት ሳይነኩ የማዘጋጃ ቤቶች ማህበራት የሚከተሉትን ይፈጽማሉ።

1. በሀብት፣ በተሞክሮና በኃላፊ ልውውጥ ዘዴዎች በመጠቀም የማዘጋጃ ቤቶችን የእርስ በእርስ ትብብር ማራመድ።
2. እንደ ሥልጠና ቁሳቁስና ገንዘብ ነክ ድጋፎች ባሉት ግብአቶች አማካይነት ለአባል ማዘጋጃ ቤቶች የአቅም ግንባታ እገዛ ማድረግ።
3. የሥነ ምግባር ደንብ ማዘጋጀት፣ ማውጣትና መከበሩን ማረጋገጥ፣
4. ለማዘጋጃ ቤቶች ሥራ አመራር የሚረዱ የጋራ ደረጃዎችና መመሪያዎችን አውጥቶ በሥራ ላይ ማዋል።
5. ከሃገር ውስጥና ከውጭ ማዘጋጃ ቤቶች ማህበራት ጋር የሚደረጉ መልካም የሥራ ግንኙነቶችን ማራመድ።
6. በክልሉ ውስጥ የከተማ ልማትን የሚያፋጥኑ ሌሎች ተግባራት ማከናወን።

ምዕራፍ ዘጠኝ

2. Notwithstanding the provisions of Sub-article 1 hereof, the regional Executive committee governing municipal judicial administration afterwards shall issue regulations.

Chapter Eight
Municipal Associations

28. Establishment of Associations

1. Municipalities shall have the right to establish and organize municipal associations and actively participate in their operations;
2. Five or more municipalities in an administration zone may form and establish a basic municipal association.
3. Municipalities in an administrative zone which are less than five in number may establish and form inters zonal basic associations.
4. Zonal and interposal basic associations may jointly establish and form a Region-wide municipal association.
5. Municipal associations may have their own constitutions

29. Registration

Zonal, Interzonal and Regional municipal associations shall be registered with the Regional Bureau of Works & Urban Development.

30. Functions of Municipal Associations

Municipal associations shall, among other things perform the following functions:

1. Promote inter-municipal cooperation through the exchange of resources, experiences and ideas;
2. Assist in building of the capacity of its members through such inputs as training, material and financial support;
3. prepare and issue a code of conduct and ensure its observance there of;
4. set and implement common standards and guidelines for municipal management;
5. promote good working relations with local and over-seas municipal associations;
6. Carry out such other functions as may promote municipal development in the region.

Chapter Nine

339

339

ስለከተማ ፕላን

31. የፕላን ዝግጅት

1. ማናቸውም ማዘጋጃ ቤት በክልሉ መንግሥት አስቀድመው የተቀመጡ የፕላን መርሆዎችንና ለሥራው የተደነገጉ መስፈርቶችን ተከትሎ የራሱን የከተማ ፕላን የማዘጋጀት ወይም እንዲዘጋጅ የማድረግ ስልጣን አለው::
2. የከተማው ነዋሪዎች ሂደቱ እንዲጀመር ማነሳሳትን፣ ጥናትና የፕላን ዝግጅት ክለሳን፣ አጽድቆትና በሥራ ላይ ማዋልን ጨምሮ በከተማው ፕላን ሥራ ጉዳይ በየደረጃው የመሳተፍ መብት ይኖራቸዋል::
3. የከተማው ም/ቤት ከቢሮው ጋር ተገቢውን ምክክር በማድረግ የከተማው የእድገት ፕላን የሚያዘጋጅለት የራሱ አማካሪ ሊሰይም ይችላል::
4. የፕላን ዝግቱ ሂደት የሚከናወነው ከቢሮው ጋር በሚደረግ የቅርብ ትብብር ይሆናል::

32. ስለፕላን አፀዳደቅና ተፈጻሚነቱ

የከተማው ምክር ቤት የከተማውን ፕላን የማፅደቅና በአግባቡ በሥራ ላይ መዋሉን የመከታተል ሥልጣን ይኖረዋል::

ምዕራፍ አሥር
የቢሮ ሥልጣንና ተግባራት

33. መሠረቱ

በሌሎች ህጎች የተሰጡት ሥልጣንና ኃላፊነቶች ሳይነኩ ቢሮው የማዘጋጃ ቤቶችን ተግባርና ሁለንተናዊ እድገት የሚፋጠን ጥረቶቻቸውን የሚስተባበርና የመደገፍ፣ ለከተሞች የወጡ ደረጃዎችና መመዘኛዎች በአግባቡ መከበራቸውን የማረጋገጥና የክልሉን መንግሥት በከተማ ነክ ጉዳዮች የማማከር ኃላፊነት ይኖርበታል::

34. ልዩ ተግባራትና ኃላፊነቶች

ከዚህ በላይ በአንቀጽ 33 የተነገረው ጠቅላላ ድንጋጌ ሳይነካ ቢሮው፣

1. ህጋዊ ሰውነት ይዞ መደራጀትና የማዘጋጃ ቤት አጀም ማግኘትን አስመልክቶ የሚነሱ ጥያቄዎችን መርምሮ በመወሰኑ ረገድ ግንባር ቀደም አካል ሆኖ ይሠራል::
2. እንደሥልጠና፣ ግንዛቤ ማዳበሪያና የልምድ ልውውጥ ፕሮግራሞች ባሉ ቴክኒካዊ ግብአቶች የማዘጋጃ ቤቶች አቅም እንዲጎለብት በቅርብ ሆኖ ይረዳል::
3. በመንግሥትና በማዘጋጃ ቤቶች መካከል መልካም የሥራ ግንኙነቶችን ያፋጥናል፣ ያስፋፋል::
4. ማዘጋጃ ቤቶች ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጪ አገር ከተሞች ጋር ግንኙነቶች እንዲመሠርቱ ያግዛል:: ስለሚያስገኛቸው ጥቅም ያላውቃቸዋል::

Urban Planning

31. Plan Preparation

1. Every municipality shall have the authority to prepare or cause to be prepared its own urban plan following the planning principles and standards laid down for the purpose by the Regional State.
2. The residents of the municipality shall have the right to participate in all stages of the planning process; including the initiation of the process, the study for and the actual preparation, revision, approval and implementation of the plan.
3. The municipal council may, in appropriate consultation with the Bureau, designate its own consultant to prepare the city development plan;
4. The plan preparation process shall be conducted in close cooperation with the Bureau.

32. Approval and Implementation of the Plan

The municipal council shall have the authority to approve the plan and oversee its proper implementation.

Chapter 10
Powers and Duties of the Bureau

33. Principle

Without prejudice to the powers and responsibilities assigned to it by other laws, the Bureau shall be responsible for facilitating the operation and overall development of municipalities, coordinating and supporting their efforts, ensuring the proper observance of urban standards and advising the Regional State on municipal affairs.

34. Specific Duties and Responsibilities

Without limiting the generality of art. 33 hereof, the Bureau shall:

1. being the lead agency in the examination and determination issues pertinent to incorporation and municipal status;
2. assist raise the capacity of municipalities through such technical inputs as training, awareness raising and experience sharing programs;
3. facilitate and promote good working relationship between the government and municipalities;
4. assist municipalities establish contacts with cities in and outside the country and make them aware of the benefits that they would gain;

5.የከተማውን ሁለገብ እንቅስቃሴ ለማስፋፋት በማሰብ የምርምርና የልማት ሥራዎችን ያካሂዳል።

6.ከተማ ነክ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ደንቦችን ያመነጫል፣ ደረጃዎችን ያወጣል።

7.ከተሞች ለወጡ ደንቦችና የጋራ ደረጃዎች ያላቸውን ተገዥነት ያረጋግጣል። ማዘጋጃ ቤቶች ኃላፊነቶቻቸውን በብቃት እንዳልተወጡ ሲደርስበት ደግሞ ተገቢ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል።

8.የማዘጋጃ ቤቶች የእድገት ፕላን ከአጠቃላዩ የክልሉ ዕድገት ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል።

9.የበጀት ዝግጅትና አፈጻጸምን፣ የድርጊት መርሃ ግብርን፣ የከተማ ፕላንን፣ የለው ኃይል ስምሪትን፣ የገቢ አሰባሰብንና አስተዳደርን አስመልክቶ ማዘጋጃ ቤቶች የሚያስፈልጋቸውን ቴክኒካዊና ሙያ ድጋፍ ይሰጣል።

10.በማዘጋጃ ቤቶች የሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያተኮሩ ዘገባዎችን በየወቅቱ ለክልሉ መንግሥት ያቀርባል።

11.የማዘጋጃ ቤቶችን ማህበራት ይመዘግባል፣ ያስተዳድራል፣

12.ማዘጋጃ ቤቶችን በሚጠቅም መልኩ ለከተሞች ጥብቅና የመቆምና ድጋፍ የማሰባሰብ ሚና ይጫወታል።

ምዕራፍ አሥራ አንድ
የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

35. ከመንግሥት ጋር ስለሚኖሩ ግንኙነቶች

በከተማ ውስጥ ተቋቁሞ የሚገኝ ማናቸውም ቀበሌ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 ሥር በተደነገገው መሠረት ለተገቢው የማዘጋጃ ቤት ሹም በቀጥታና በብቸኝነት ተጠሪ ሊሆን እስከሚችልበት ጊዜ ድረስ በማዘጋጃ ቤትና አሁን በሚገኘው የመንግሥት መዋቅር መካከል ያለው ግንኙነት እንደሚከተለው ይሆናል።

1.የከተማ ቀበሌዎቹ የምርጫ ጣቢያዎች ሆነው የሚያገለግሉባቸው የከተማ ምክር ቤት ምርጫዎች ይካሄዳሉ።

2.ይህ አዋጅ በሚጸናበት ጊዜ፣ እስከ አሁን ድረስ ተቋቁመው ሲሠሩ የቆዩት ቀበሌዎች፣ የከተማ ወረዳዎችና የባህር ዳር ልዩ ዞን መስተዳድር የማዘጋጃ ቤቶች ምርጫ እንደተጠናቀቀ በባህሪያቸው ከተማ ነክ የሆኑትን ሥልጣንና ኃላፊነቶቻቸው በሙሉ አዲስ ለሚቋቋሙት የከተማ ምክር ቤቶች ያስረክባሉ።

3.ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 2 የሰፈረው ድንጋጌ ቢኖርም ቀበሌዎቹ ከማዘጋጃ ቤቶች ጋር በዚህ አዋጅ መሠረት በሚፈጥሩት ግንኙነት ማከናወናቸው

5.Undertake research and development works with the view to promoting an all out urban progress;

6. initiate regulations and issue standards pertaining to municipal affairs;

7.ascertain the adherence of urban centers to regulations issued and common standards set; ensure the taking of appropriate measures where municipalities fail to discharge their responsibilities;

8.Ensure that the development plan of municipalities conform with the overall development plan of the region;

9. provide technical and professional support to municipalities with regard to the preparation and execution of their budget, plan of action, town planning, allocation of manpower and collection and administration of revenues.

10.Submit periodic reports to the Regional government on the activities of municipalities;

11.Register and administer associations of municipalities

12. Play the role of an advocate and a lobbyist in the best interests of municipalities;

Chapter Eleven
Transitory Provisions

35. Relations with the Government

Until such time that the urban Kebele is made directly and solely accountable to the pertinent municipal authority as envisaged under article 14 hereof, the relationship between the municipality and the existing state structure, shall be as follows:

1.Municipal elections shall be held with urban Kebeles serving as polling stations

2.Urban Kebeles, urban Woredas and the Bahar Dar Special Zone as they exist on the coming into force of this proclamation shall, after the municipal elections are through, hand over to the municipal councils all powers and responsibilities considered to be municipal by nature. Urban Woreda Councils and the Bahar Dar Special Zonal Administration shall continue to perform state functions.

3.Notwithstanding the provisions of sub-article 2 hereof, Kebeles shall continue to perform state functions as stipulated for in the constitution of the Amhara National Regional State, provided

341

341

እንደተጠበቀ ሆኖ በአግራ ብሔራዊ ክልል ህገ መንግሥት በተመለከተው አኳኋን መንግሥታዊ ኃላፊነታቸውን መፈፀም ይቀጥላሉ።

4. ቀበሌዎች ለመንግሥታዊ ሥራ አፈጻጸም ተጠሪነታቸው ለታቀፉበት ወረዳ ም/ቤት ሲሆን በከተማ ነክ ጉዳዮች ደግሞ ለሚመለከታቸው ማዘጋጃ ቤቶች ይሆናል።

36. ስለሰው ኃይል አስተዳደር

1. የማዘጋጃ ቤቶች የሰው ኃይል አስተዳደር ህግ ወደፊት ወጥቶ ሥራ ላይ እስከሚውልበት ጊዜ ድረስ የማዘጋጃ ቤት የሰው ኃይል አስተዳደር ጉዳዮች የማዘጋጃ ቤቶች የሰው ኃይል አገልግሎት ቦርድ በሚያወጣው ጊዜያዊ የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት የሚስተናገዱ ይሆናሉ።

2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተጠቀሰው ጊዜያዊ የአፈጻጸም መመሪያ የህገራቱን ፌደራላዊ እና ክልላዊ የሠራተኛ ጉዳይ ፖሊሲዎችንና ህጎች የማዘጋጃ ቤቶችን ሁለንተናዊ አትምና እንዲሁም የስልጣንና ኃላፊነታቸውን ልዩ ባህሪ ግምት ውስጥ በማስገባት የሚዘጋጅ ይሆናል።

37. ስለማዘጋጃ ቤቶች የዳኝነት አካል

ማናቸውም ማዘጋጃ ቤት የራሱን ፍርድ ቤት እስከሚያቋቁምበት ጊዜ ድረስ ከዚህ በታች የሠፈሩት የመሸጋገሪያ ሥርዓቶች በቅድሚያ ወጥተው ሲሠራባቸው ይቆያሉ።

1. ከተማ ነክ ፍ/ቤቶች በቀዳሚነት የሚቋቋሙት በተመረጡ የእርከን ሶስት ማዘጋጃ ቤቶች ክልል ብቻ ይሆናል።

2. አግባብ ባለው መንገድ የተቋቋሙ ከተማ ነክ ፍ/ቤቶች ከሚከተሉት ክፍሎች የሚነሱ ማዘጋጃ ቤት ነክ ጉዳዮችን ይዳኛሉ።

ሀ. ጉዳዩ ከሚመለከተው ማዘጋጃ ቤት ለይፍርድ ቤቱን ዋና መቀመጫ የሚዋሰኑ ሌሎች ማዘጋጃ ቤቶች ጥያቄ ሲያቀርቡ፣

3. ልዩ ልዩ ተዘዋዋሪ ችሎቶች እንዳስፈላጊነቱ ይቋቋማሉ፣

4. ማናቸውም ማዘጋጃ ቤት የራሱን ከተማ ነክ ጉዳዮች ለመዳኘት የወጣውን ወጪ ድርሻ የመሸፈን ግዴታ አለበት።

5. በአዲስ መልክ የተቋቋሙት ከተማ ነክ ፍ/ቤቶች በመደበኛ ሥር ከሚገኙት የአገልግሎት ማቀላጠፊያ መሣሪያዎች፣ የሰው ኃይልና ቁሳዊ ኃብቶች የሚጋሩበት ሥርዓት ከክልሉ መንግሥት ጋር በሚደረግ ምክክር ይመቻቻል።

6. የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች ባልተቋቋሙባቸው ማዘጋጃ ቤቶች ከተማ ነክ ጉዳያቸው በመደበኛ ፍርድ ቤቶች መታየቱን ይቀጥላል።

ምዕራፍ አሥራ ሁለት

however that they shall also perform municipal functions by an arrangement with municipalities.

4. Kebeles shall be accountable to the Woreda councils for state functions; provided however that, they shall also report to their respective municipalities on municipal matters.

36. Personnel Administration

1. Until such time that the municipal personnel service law will have been developed and enacted, the personnel administration affairs of a municipality shall be governed by provisional guidelines to be issued by the Municipal Personnel Service Board.

2. The provisional guidelines referred to under sub-article (1) hereof shall be prepared taking into account Federal and Regional labour and civil service policies and legislation, the overall capacities of municipalities and the special nature of their powers and responsibilities.

37. Municipal Tribunal

The following transitional arrangement shall in advance come into effect and remain in force until such time that every municipality is able to establish its own municipal tribunal:

1. Municipal tribunals shall first be established only in selected grade III municipal areas;.

2. Municipal tribunals duely established shall adjudicate municipal cases which may arise from the following sections:

a. the municipality establishing the same;

b. other municipalities adjacent to the principal seat of the tribunal; provided that such municipalities so request.

3. Circuit divisions may be established when deemed necessary;

4. Every municipality shall bear its share of the expense incurred in the cost of adjudicating of its municipal cases.

5. Arrangements may be made with the Regional state whereby newly established municipal tribunals may have access to the facilities and human and material resources within the power of regular courts.

6. In municipal areas, not yet establishing municipal tribunals, municipal cases shall continue to be adjudicated by regular courts.

Chapter 12

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

38. አዳዲስ አሠራሮችን ስለመሞከር

1. በማናቸውም ደረጃ የተቋቋመ ማዘጋጃ ቤት ቢሮውን በማማከር ራሱን ለማደራጀት ሥልጣኑን ሥራ ላይ ለማዋል ወይም ከተማ ነክ ተግባራትን ለመፈጸም የሚያስችሉ አዳዲስ ዘዴዎች እያፈለቀ ሊለማመድ ይችላል።
2. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር ለተጠቀሰው የሙከራ ተግባር የጊዜ ገደብ ከማበጀት ባሻገር ውጤታማነቱን ለመወሰን የሚያስችል ወቅታዊ ግምገማዎችን ሊያካሂድ ይችላል።

39. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚያስፈልገውን ደንብ የማውጣት ሥልጣን የክልሉ መንግሥት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይሆናል።
2. ለዚህ አዋጅና ደንብ አፈጻጸም የሚያስፈልገውን መመሪያ የማውጣት ሥልጣን የቢሮው ይሆናል።

40. ስለተሻሩ ህጎች

በሌላ ሁኔታ በግልፅ ካልተደነገገ በስተቀር ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ሲሠራባቸው የቆዩ፣ የተጻፉም ሆነ ያልተጻፉ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱ ጉድዮች ላይ ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው በዚህ አዋጅ ተተክተዋል።

41. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር
የካቲት 30 ቀን 1992 ዓ.ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት

Miscellaneous Provisions

38. Experimentation

1. A municipality established at any grade may, in consultation with the Bureau, innovate and experiment new ways of organizing itself, exercising its powers or performing municipal functions.
2. The Bureau may apart from setting a time limit for the experimentation referred to under sub-article 1 hereof, conduct periodic evaluations to determine its efficacy.

39. Power to Issue Regulations and Directives

1. The executive committee of the regional State may issue regulations necessary for the implementation of this proclamation.
2. The Bureau may issue directives necessary for the implementation of this proclamation and regulations there under.

40. Inapplicable laws

Unless otherwise expressly provided, all laws, rules, regulations, and directives whether written or otherwise previously in force shall be of no effect as regardes matters provided for in this Proclamation.

41. Effective Date

This proclamation shall enter into force as of the day of its publication on the Zikre Hig Gazetta.

Done at Bahir Dar
This 9th day of March 2000
Council of The Amhara National Regional State.

343

343